# ወ ቅ ዷ ለ

የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (ዐኅኢአድ) ልሣን



የዐማራ ኅልውና መጠበቅ፣ ለኢትዮጵያ አንድነት መጠበቅ ዋስትና ነው!

ፈለገ አሥራት የትውልዳችን ቃል ኪዳን ነው!

ቅጽ: ፩ ቁጥር: ፫ ቀን: ጥር ፲፯ ፪ሺ፲

በየ15ቱ ቀን ዘወትር ኀሙስ የሚወጣ


## ምርጫው በባርነት መቀጠልና በነፃነት መካከል ነው!

ኢትዮጵያ ሀገራችን በወያኔ ትግሬ ዘረኛ አገዛዝ እየተናጠች ነው። ወጣት ልጆቿ መሪር መስዋዕትነትን እየከፈሉ ነው። አበው የተወለዱበትን ቀን እየረገሙ የሚተክዙባት፣ ወላጅ እምቡጥ ልጆቹን የሚቀብርባት ሀገር ሆናለች። ፈጣሪ ምን መዓት አመጣብን የሚያስብል የማያልቅ የሚመስል የፍጅት አዙሪት ውስጥ የገባች ሀገር ሆናለች። እነዚህ የሕዝባችን የሥቃይና የፍጅት የእሮሮ መገለጫዎች የትግሬ ወያኔ የእልቂት አዝመራ መገለጫዎች ናቸው።

ይህ አረመኔ የትግሬ ባንዳ የተከለብን የከፋፍለህ አባላው ሥርዓት ወደ መቃብር ጉዞው ላይ በመሆኑ በዚያው መጠን የሚሰነዝረውም የአጥፍቶ መጥፋት ግብግብ ርኅራኄ ቢስ ነው። አላፊ አግዳሚውን እየተኮሰ የሚጥል አውሬ ነው። ይህ አውሬ ላንዴና ለሁሌ በማያዳግም ሁኔታ ከዚች ቅድስት ሀገር መደምሰስ ይኖርበታል። ዛሬ ይህ የኛ በዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ሥር የተሰለፍን ልጆቿ አቋም ብቻም ሳይሆን፣ የመላው ሕዝብ የማያወላውል አቋም ሁኗል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ከትግሬ ወያኔ ጋር ላያድር ተማምሎ ለትግሉ መስዋዕት ለመሆን አደባባይ ወጥቷል። ይህ የማይታጠፍ አቋም ሆኖ እንዲዘልቅ፣ ከሕዝቡ ጎን መቆም ኢትዮጵያዊ ነኝ ከሚል ሁሉ የሚጠበቅ ነው።

ይሁንና፣ ይህ የሕዝባችን አቋም አቋማቸው ያልሆኑ ተማርን፣ ዐወቅን ተብዬዎች እንዳሉም ሊታወቅ ይገባል።

# ምርጫው በባርነት መቀጠልና በነፃነት መካከል ነው!

የችግሩ ምንጭ የትግሬ ወያኔን በማወቅ እሱና መሰሎቹ የተከሉት ዘረኛና የከፋፍለህ አባላው ሕገመንግሥት ተብዬ ሳይሆን፣ "የዲሞክራሲያዊ አለመኖር የወለደው ችግር ነው" ብለው ሕዝቡን በቅብብሎሽ በባርነት ለመግዛት የቋመጡ መኖራቸው እውነት ነው። ሕገመንግሥቱ እንከን የለውም፤ አንዳንድ መቀባባቶች ተደርገውበት ዲሞክራሲያዊ ማድረግ ይቻላል ይሉናል። ሕዝብን በዘር ልዩነት ላይ ያዋቀረ ሕገመንግሥት እንዴት ሁኖ ነው ሁሉንም ነገሮች በአንድ ዓይን ማየት የሚችል ዲሞክራሲያዊ ሥርዓርት የሚሆን? ጉልበተኛው ዘረኛ፣ ትንሹን ዘረኛ አስደግድጎና አስገብሮ ሲገዛው እነዴት ሁኖ በመሀላቸው ያለ ግንኙነት ዲሞክራሲያዊ ሊሆን ይችላል? በጠባቡ የጎሳው አባላት እንኳን ያልተመረጠ አዲሱ የገዢው መደብ የራሱን የጎሳ ሕዝብ በባርነት በያዘበት ሁኔታ እንዴት ዲሞክራሲያዊ አስተዳደር መመሥረት ይቻላል? ይህን መሰሉ ዛሬ ባይናችን ፊት ተገትሮ የምናየው ገሐድ ነው። ይህ የከፋፍለህ አባላው ሥርዓት፣ ሁሉም እንደ ሥራ ውጤቱ ሳይሆን፣ እንደ የአቅሙ ተቀራምቶ ዘርፎ የሚታደርበት አገዛዝ መሆኑን ወያኔዎቹ ራሳቸው አልካዱም። ሥርዓቱ የሕዝባችን ደግና የበዙ አስተሳሳሪ ዕሴቶችን አጥፍቶ፣ በጥቂት ልዩነቶቻቸው ላይ እራሱን የገነባ ሥርዓት በምንም ተዓምር ዲሞክራሰያዊ ሊሆን አይችልም።

የሕዝባችን ሸጋና ልዩ ዕሴቶች አንተ ትብስ አንተ ተባብሎና ተቻችሎ፣ ተጠጋግቶና ተረዳድቶ አብሮ የመኖር ታሪኩ፣ ከባህልነትና ከእርሱነቱ መገለጫነት ዘልቆ ሰብአዊ ባሕሪይው ነው። ዲሞክራሲ በዚህ ደግ የሕዝብ ውብ፤ ድንቅና ታላቅ ዕሴት ላይ ሲመሠረት ብቻ ነው ፍሬ ሊያፈራ የሚችል። በትግሬ ወያኔና በኦነግ ተረቆ፣ የጥፋት ዘሩን ዘርቶ ፍሬውን እየሰበሰበ በሚገኝ ሕገመንግሥት ተብዬ ዲሞክራሲን ማሰብ ከቶ አይቻልም። «ይህ ሕገመንግሥቱ ችግር የለበትም፣ ችግሩ ዲሞክራሲያዊ አመራር አለመኖር ነው» የሚሉ ወገኖች፣ ቀደም ሲል ጀምረው የቆሙለት ዓላማ ኢትዮጵያዊው ዜጋ በረጅም ታሪኩ ገንብቶት የመጣውን የመደጋገፍ፣ የመቻቻል፣ የአብሮነትና የኢትዮጵያዊነት ሕዝባዊ መሠረት ያላቸውን ዕሴቶች የማፈራረሻ ሁነኛ መሣሪያቸው እንደሚሆን ስለተገነዘቡ ነው። ይህ እንዲቀጥልም ሽንጣቸውን ገትረው ሲከራከሩ እናያለን። ሕዝብን ለያይቶ፣ የሚያገናኙትን መልካም ዕሴቶችን በጣጥሶ ሕዝቡን በባርነት ሥር ጥሎ ለመግዛት ለመጣ አውሬ ከዚህ የተለየ ፍቱን መንገድ አልነበረም። እናም ላለፉት 27 ዓመታት የሆነው ይህ ነው። በዐማራ ኀልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅትና ሕዝብ በአንድ በኩል፣ በሌላ በኩል ለትግሬ ወያኔ ዘረኛ ሕገመንግሥት መቀጠልና ከባንዳው ጋር ለመደራደር በቆሙት ቡድኖች መካከል ያለው ልዩነት ግልጽ ሆኖ ወጥቷል።

# ምርጫው በባርነት መቀጠልና በነፃነት መካከል ነው!

ምርጫው በባርነት መቀጠልና በነፃነት መካከል ያለ ልዩነት ነው። ዛሬ የጥገና ለውጥን የሚናፍቁ “መንግሥት እራሱን ወደ መሀል መንገድ ማምጣትና ከተቃዋሚው ጋር መደራደር አለበት” በሚል በሚገባ ተገልጧል። መንግሥት ተብዬው ፋሺሽት ወያኔ መሆኑ ነው። የሚፈሰው ደም የዶሮ ደም ያህል የማይቆረቁራቸው ከመእንሰሶች! ለጥገና አራማጆች የሀገሪቱ ሉዓላዊ ግዛት እነሱ እንዳይፈርስ ከሚጨነቁለት “ክልል” በጣም የራቀና እነሱን የማይመለከት ጥያቄ ነው። እናም ከወያኔ ጋር እንዲሆን የሚፈልጉት ውይይትና የሚያወሩት ሥልጣን የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚያካትት ሳይሆን፣ ክልላቸውን ከመፍረስ ለማዳን የሚደረግ “ድርድር” መሆኑ ነው።

የሽግግር ቻርተር የሚሉት ሰነዳቸው የተመሰረተው ከዚህ ጠባብ የባለህበት እርገጥ አመለካከት መሆኑም አይደንቅም። ለሽግግሩ መነሻ አድርገው የሚያቀርቡት ጨፍጫፊው የትግሬው ወያኔ ጥሪ እንዲያደርግላቸው ነው። ወደ መሀል መንገድ ግባ የሚለው ጥሪ ትርጉም ይህ ነው። አንተም ከጥፋት ጉዞህ ተመለስ፣ እኛንም በሕዝቡ ፊት አታጋልጡን፣ የጋራ ጥቅማችንን አንጣ በሚል ቢቀመጥ የጥሪውን እምብርት በሚገባ ይገልጠዋል። የጥገና ለውጥ ማለት ሕዝቡን ያገለለ፣ ዳግም ለሌላ የአምባገነኖች አገዛዝ ሥር ጥሎ፣ ደሙን ሊመጥ የተዘጋጀና የድርጅቶች ጥምሮሽ የሥልጣን እርክክቦሽ የሽግግር ጊዜን እውን ማድረግ ነው። እነዚህ የዛሬዎቹ የጥገና ለውጥ ጠያቂዎች ለሕዝባችን አዲስ አይደሉም። ከዚህ በፊት በዚሁ የከህደት አደባባይ ላይ ቁመው ተመልከቷቸዋል። ለሕዝባችን ሚስጢር አይደሉም። እናም ለነሱ ትግሉ ከወያኔ መውደቅ አልፎ ሥርዓቱን እንዳለ ከጥፋቱ ለማዳን የሚደረግ ትግል ቢሆን ምን ይደንቃል?

የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ከዚህ ኋላ ቀር፣ ለሕዝባችን አንድነት ፀርና ለሀገራችን ሉዓላዊነት አደገኛ ከሆነ መስመር በተቃራኒው የቆመ ድርጂጅት ነው። የዘረኛው ሥርዓት ከነፈጣሪው የትግሬ ወያኔ ጋር መወገድ አለበት ይላል። የድርጅታችን እምነት የሽግግር ጊዜው መመራት ያለበት እራሱ ሕዝቡ በሚመርጣቸው ወኪሎቹ መሆን አለበት ። ከዚህ ሕዝባዊ የሽግግር መንግሥት የሚወለድ ቋሚ የሀገሪቱ መስተዳደር ያለምንም ጥርጥር ዲሞክራሲያዊ ይሆናል ብለን እናምናለን። ላለፉት 47 ዓመታት ሳያቋርጥ የመጣው የናውቅልሃለን የምሁራን አምባገነን አገዛዝ አዙሪት የሚሰበረው በዚህ እርምጃ ብቻ ነው ብለን እናምናለን።

# ምርጫው በባርነት መቀጠልና በነፃነት መካከል ነው!

ለሕዝባችን የቀረበው ምርጫ ቀላልና የማያሻማ ነው። ባርነትን ወይም ነፃነትህን የመምረጥ ጉዳይ ነው። የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት የቆመው የሰው ልጅ ሁለንተና ነፃነቱን በጁ እንዲያደርግ ነው። የኛ ትርፉችን ይህና ይህ የሕዝቦች ኅልም እውን ሁኖ ማየት ነው። በሕዝባችንም ውሳኔ ትክክለኛነት አንጠራጠርም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ፊደል የመቁጠር ዕድሉን ሳያገኝ ቀድሞ መሄጃውን አጥርቶ ያወቀ ሕዝብ ነው። በማያልቅ ትዕግሥቱ ምክንያት መከፈል የሌለበትን መስዋዕትነት እንዲከፍል የሆነ ሕዝብ ነው ። ካሁን በኋል ግን ዳግም በአምባገነኖች ሥር ላለመውደቅ አምርሮ የተነሳ ሕዝብ መሆኑንም ባደባባይ እያሳየ ያለ ሕዝብ ነው። ከጀመረው የትግል ጉዞው ማንም እንደሚመለከተው ትግሉ ለጥገና ሳይሆን፣ ለመሠረታዊ ለውጥ መሆኑ ሊያዝ ይገባል። እኛም በዚህ እሱ በመረጠው የትግል ጎዳና ተሰልፈን እስከመጨረሻ ግብ ድረስ አብረነው ለመጓዝ ቃል ገብተን ተነስተናል። ለዚህ ግብ በዓላማ ከሚመስሉን ጋር በመሰባሰብ ትግሉን ለማጠናከር ቃል እንገባለን።

የዐማራ ኅልውና መጠበቅ ለኢትዮጵያ አንድነት መጠበቅ ዋስትና ነው!

ውድ እናት ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!!